# ይድረስ ለገዢው ፓርቲ
# ይድረስ ለተቀዋሚ ፓርቲዎች
# ይድረስ ለገለልተኛ ኢትዮጵያውያን

(ዮሴፍ ወ. ደግፌ)
ጉዳዩ:- "ቤት በጥበብ ይሰራል፥ በማስተዋልም ይጸናል፥"

ቤት በጥበብ እንጂ በጠብ እንደማይሰራ፥ በማስተዋል እንጂ በስሜታዊነት እንደማይጸና፥ መፅሀፍ ቅዱስ በመፅሀፈ ምሳሌ ምዕ. 24 ቁ. 3 ላይ ያስተምራል … 'ቤት በጥበብ ይሰራል' በሚልበት ጊዜ ሰዎች በጋራ የሚመሰርቷቸውን ቤተሰባዊ መንፈሳዊ ሀገራዊና፥ የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህብረቶችንና ተቋማትንም ሁሉ የሚያጠቃልል ነው … የጋራ ቤትን ለመገንባት የጋራ ራእይ ማውጣት፥ አላማን መንደፍ፥ ግቦችን መተለም የሚያስፈልግ ሲሆን ... በሂደት በሰዎች መካከል የአመለካከት ልዩነት ሊፈጠር ስለሚችል … አላማንና ግቦችን የማያስት እስከሆነ ድረስ፥ በመቻቻል በመደራደር መስራት (Compromising) ጥበብና ማስተዋል ደግሞም ስልጡንነትና ዲሞክራሲዊ አካሄድ ነው። … በተቃራኒ ሀሳቦች በመደራደር የዳበረ ውይይት … በሳል ውሳኔን በማመንጨት ... መተማመንን በማዳበር ... ህብረትን አንድነትን በማጠናከር እንዲሁም አሰራርን በማጠናከር ሂደትን የማፋጠን አቅሙ ከፍተኛ ነው ... ልዩነትን አቻችሎ መስራት የአብሮነት ውዴታ ግዴታም ነው።

ካናዳዊ የባህርይ ጥናት ሳይኮሎጂስት (Behavior psychologist) አልበርት ባንዱራ ባደረገው የማህበራዊ ባህርይ ጥናት (Social Behavior study) ሰዎች ከሚያደረጉዋቸው 20 ውይይቶች 17ቱ (85%) ግብብነት የሌላቸው የሚቃረኑ ሃሳብዎች (negative communications) እንደሆኑ አረጋግጦአል። … ይህም የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሮአዊ ሰውኛ (Humanistic) ነው ወደሚል መደምደሚያ ይወስዳል። … ታዲያ ሰዎች በጋራ አጀንዳ ላይ እየተደራደሩ ከመኖር ውጭ ምን የተሻለ ምርጫ አላቸውና ነው በመጣላት የሚበታተኑት?

ከአለም ህዝብ 10% በታች የሚሆኑት ምእራባውያን በጋራ እየተደራደሩ በመስራት ‘ባለመግባባትም ቢሆን ተገባብተው' (‘agree to disagree’) ሁለንተናዊ አቅማቸውን በማሳደግ በኢኮኖሚ በፖለቲካና በወታደራዊ የበላይ ሆነው አለምን ይመራሉ ... አፍሪካውያን ግን ዛሬም ድረስ ካልተግባባን መጨራረስ ያለብን ይመስል እንደ አይጥና ድመት እየተጠባበቀን በጦርነት እንደ ቅርጫ ስጋ እየተከፋፈልን/እየተበታተንን/ አቅም በማጣት እንዳከራለን። ... በተራ አለመግባባት ችግር ምክንያት በከፋ መቃቃር፥ በጸብ … በቂምና በጥላቻ በመለያየት፥ ብዙ የተወጠነበትንና የተደከመበትን ቤተሰባዊ፥ መንፈሳዊ፥ ማህበራዊ ፖለቲካዊ ሀገራዊ ህብረት በቀላሉ በማፍረስ፥ አንዳችን አንዳችንን አጥፍተን በ"ሰላም" ለመኖር እንጥራለን፥ (አንዱን አንዱን አጥፍቶ በሰላም ለመኖር አይችልም እንጂ) በተለይ ኢትዮጵያውያን በጋራ አጀንዳ ላይ እየተደራደርን ተግባብተን መስራት ለምንድነው የሚያቅተን?

የተለየ የግል አላማ ከሌለ በስተቀር የሀሳብ ልዩነቶች በተሻለ አማራጭና መፍትሄ አምጪነት እንጂ፥ በአፍራሽነት በመመልከት፤ በጋራ አጀንዳ ላይ ለድርድር እንቢተኛ መሆን ኢ-ዲሞክራሲያዊነት ወይም አምባገነንነት ነው። ... በራእይ በአላማና እንዲሁም በግብ አንድ ሆነው ሳለ … በሃሳብ ልዩነቶቻቸው ላይ መደራደር እያቃታቸው ጥበብንና ማስተዋልን በማጣት በግትርነትና በስሜታዊነት በየግዜው በመሰነጣጠቅ ከሚፈርሱትና ከሚበታተኑት የኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ህብረቶች መካከል፥ …የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን፥ ... የገዢው ፓርቲ ኢሊቶችን፥ ... የዳያስፖራ ጊዜያዊ ፖለቲካ ማህበራትን፥ ... የዳያስፖራ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲዎችን፥ ... የዳያስፖራ የኢትዮጵያ ስፖርት ማህበራትን፥ … እንዲሁም የኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ መንፈሳዊ ህብረቶች ጭምር ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል።

ኢትዮጵያውያን በቤተሰብም ሆነ በት/ቤት ውስጥ እድገታችን እንዲሁም ደግሞ የመንግስታቶቻችን የአገዛዝ ባህርይ በውይይት/ድርድር ሳይሆን፥ ‘በገዢና በተገዥነት’ ... ‘በበላይና በበታችነት’ ... ‘ትእዛዝ በመስጠትና መመሪያ በመቀበል’ … ‘በአለቃና በምንዝር’ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ … ስሜታዊ እድገታችን ተጨፍልቆ በባህርያችን ላይ ትልቅ ተፅእኖ በማሳደሩ በውይይት በክርክርና በመደራደር የጋራ ስምምነት ውሳኔ ላይ ለመደረስ የሞት ያህል ይከብደናል … ለመግባባት አለመቻላችን ከግል አልፎ ሀገራዊ ጉዳትና ጠባሳ እየተወ ይታያል። …ድርጅታዊ ተቋም ካለንም ተቋማዊ ህገ-ደንብ (መተዳደሪያ ደንብ) (By-law) በማይፈቅደው … ጠቅላላ አባላት (ጉባኤ) ሳያውቀው (ሳያፀድቀው) ከ"እኛጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመናል" በማለት … በአመለካከት የተለዩንን ሰዎችን እንደ ጠላት በመፈረጅ፥ ወደ ተከላካይነትና አጥቂነት እንቀየራለን … የእኛን ሀሳብ የሚጋራ ደካማ ደጋፊ (Cliques) ካገኘንም በብልጣብልጥነት ለመከረም እንገዳገዳለን እንጂ “ይቅርታ ተሳስተናል ታርቀን ተራርመን እንደገና አብረን እንቀጥል” ሞት ቢመጣ አንልም። … በመሆኑም ብዙ የታቀደለትንና ለመገንባትም ዘመናት የፈጀንበትን ህብረት/ተቋም በአንዲት ጀንበር አፍርሰን ቁጭ እንላለን። … ለመፍታትም አንጥርም፤ … ማንም ምንም ቢል ግድ አይሰጠንም። … ምክንያቱም ከራሳችን በስተቀር ማንንም አንሰማም … ማንንም አናምንና ነው። … ከዚህ ከተጠናወተን የባህርይ በሽታ ለመፈወስ ብዙ ትውልድ የሚፈጅብን ይመስለኛል።

ጆርጅ ፓትሰን የተባለ ሰው "… If everyone thinking alike, then somebody is not thinking…" ይላል … ሰው ሁሉ ተመሳሳይ ሀሳብ ቢኖረው ኖሮ፥ ሌላው ሰው ማሰብ አያስፈልገውም ነበር ... ምክንያቱም የአንድ ሰው ሀሳብ ለሰዎች ሁሉ በቂ ስለሚሆን ነው … ሰዎች ከአስተዳደግ ተጽእኖ፥ … ከመንፈሳዊ እምነት ተጽእኖ፥ … ከህይወት ልምድ ተጽእኖ፥ … ከትምህርት ዝግጅት ተጽእኖ Generation gap ወዘተ … የተነሳ ተመሳሳይ አመለካከት ሊኖራቸው በፍፁም ስለማይችል በድርድር-ጥበብ በማስተዋልም በጋራ መስራት ይገባቸዋል።

የዚህ ፅሁፍ አላማ የግል እይታን እንደ ዜግነት አስተዋፅኦ ማቅረብ ሲሆን 1/የየፖለቲካችን አይዶሎጂዎች/እምነቶች/መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ግን ከቡድናዊ ወይም የፓርቲ አመለካከት ነፃ በመውጣት በጋራ የምንመራባቸው የጋራ ሀገራዊ ፖሊሲዎች መቅረፅ እንደሚያስፈልገን ማስገንዘብ ነው። … … 2/በዋና ዋና ብሄራዊ ሀገራዊ አጀንዳዎቻችን ላይ የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ቡድን ራእይ አላማና ፍላጎት ብቻ በማብጠልጠል የተለየ አመለካከት ያለውን ወገን ከጨዋታ ውጪ ማድረግ ለማንኛችንም የማይበጅ ዘላቂ ስምምነት ላይ የማያደርሰን … ዘላቂ ሀገራዊ ልማትና በዋናነትም ዘላቂ ሰላም የማያመጣልን መሆኑን ማስገንዘብ ነው። … 3/የጋራ ብሄራዊ ፖሊሲዎችን (የጋራ ብሄራዊ አጀንዳዎችን) ለመቅረፅ ብሄራዊ መግባባት እንደሚያስፈልገን ማስገንዘብ ነው። …4/አክራሪ (ፅንፈኛ) የፖለቲካ አመለካከቶችን በጋራ ብሄራዊ ራእይ ለማጥበብ እንዲቻል ፖለቲከኞቻችን ወደ ማእከላዊ የፖለቲካ አመለካከት (Centrism: Centre Left or Centre Right) መምጣት እንደሚገባቸው ማስገንዘብ ነው። … በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ሁሉም የጋራ ውሳኔ የሚሰጥበት ብሄራዊ የጋራ አጀንዳ ቢኖረን ... በትንሽ በትልቁ የፖለቲካ ንትርካችን ይቀንሳል … የፖለቲከኞቻችን ውጥረት ይቀንሳል … የብልፅግና ጉዞ ዘመንም ያጥራል … 5/የጋራ ብሄራዊ አጀንዳ ለመቅረፅ በፖለቲካ አይዶሎጂ ወገናዊነት ውስጥ የሌሉ ገለልተኛ ሰዎች ... በሙስና ውስጥ የሌሉ ሰዎች... በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ... ለሀገር ትንሽ አስተዋፆ በማድረግ የሚታወቁ ሰዎች ከገዢውና ከተቀዋሚ ፓርቲዎች ጋር በህብረት እንዲሰሩት ማስገንዘብ ነው።

"እንደ እባብ ብልህ እንደ እርግብ የዋህ (?)"

10,200 ኪሎ ሜትር ያህል በመጓዝ በአለም ላይ በርዝመቱ 1ኛ የሆነውን ታላቁን የአባይን ወንዝ መሰረት አድርጎ የተገነባው የግብፅ ህይወት የአስዋን ግድብ ተገንብቶ ለግብጽ መጠነ ሰፊ ጥቅም መስጠት ከጀመረ ግማሽ ምእተ አመት (50 አመት) ሲሞላው … ኢትዮጵያ በተባለችው ምድር ላይ የሚኖረውና የአባይ ምንጭ 86% ያህል መነሻ የሆነው ህዝብ ግን … የ2ሺ አመታት መፅሀፍ ቅዱሳዊ እምነቱ እንደሚናገረው "እንደ እባብ ብልህ እንደ እርግብ የዋህ ሁን" ሆኖ ያልተገኘ ምንዱባን ህዝብ ነው። … ርግብነቱ(?) አለን ብንል እንኳን … ብልህነቱ የት አለ? … ፈጣሪ የሰጠውን የተፈጥሮ በረከቶች በመጠቀም ከርሃብና ከእርዛት ሳይወጣ ለብዙ ሺ አመታት በድህነትና በጦርነት አዙሪት ውስጥ ሲዋትት ይገኛልና። … ይበልጥ ደግሞ በግሎባላይዜሽን ዘመን ላይ አባይን በጋራ ለመገደብና ለመጠቀም የህብረት ችግር መታየቱ እጅግ አስገራሚ ነው።

በሺ ኣመታት ረጅም ታሪክዋ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው መሪዎች ህዝብ የስልጣናቸው ምንጭ ስላልሆነ ከራሳቸው አመለካከት በላይ ለሀገር ማሰብ ያልቻሉ፤ … በስልጣን ሹኩቻ በመናቆር አንዱ በአንዱ መቃብር ላይ የራሱን መንግስት በሀይል የሚገነባ፥ … የአመራር ጥበብና ማስተዋል የሌላቸው … ጆብደኞች … ግትሮች … ራስ ወዳድዎች … ባጠቃላይ አምባ-ገነንዎች በመሆናቸው የተነሳ በጦርነት የደቀቀች … ድንቁርና ርሀብና ድህነት የተንሰራፋባት ሀገርን … ደግሞም እርስበርሰ ጥላቻንና ክፋትን … ቂም በቀልን እንጂ ሌላ ምንም ውርስ አላስረከቡንም። … በመሆኑም በራሳችን ችግር ምክንያት፤ አባይንም ይሁን ሌሎች በረከቶቻችንን ለመጠቀም ባለመቻላችን፤ ለዘመናት በከንቱ በመባከን የተራቆተ ህዝብ ስለሆንን ... ሊታዘንልን እንኳን የማይገባን ነን። … ሌላው አለም ስለ እህል ማሰብ ትቶ ትልቅ ደረጃ ላይ በደረሰበት በዚህ ግሎባላይዜሽን ዘመን ላይ በአለም ፊት ርሀብተኛ ተመፅዋች ስደተኛ የድርቅና የጦርነት ምሳሌ ነን።

"ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንዲሉ አባይንም ይሁን ሌሎች ተፈጥሮአዊ ሀብቶቻችንንና የሰው ሀይል ሀብታችንን ሳንጠቀምባቸው በድህነትና በጦርነት አዙሪት (Vicious Circle of Poverty & War) ለዘመናት ስንዳክር እዚህ ደርሰናል። … እህል ሆኖ ሊጠቅመን ባልቻለ ታሪክም በባዶ ሜዳ ላይ ስንፎክርና ስናቅራራ የበረከት ምንጮቻችን ለዘመናት በከንቱ ባከኑ … ወንዞቻችንም በከንቱ ወረዱ … ከዚህ አንፃር እርዛትን እንደ ብልፅግና፥ … ርሀብን እንደጥጋብ በመቁጠር፤ … ለዘመናት እያለቅን ከንቱነታችንን ለአለም ያረጋገጥን የመሆናችንን እንቆቅልሽ በእፍረትም በድፍረትም በመናገር ለመፍታት መነሳታችን ዛሬ እንኳን ካልሆነ መቼ ሊሆን ነው?

"ኢትዮጵያውያን አብረው መብላት እንጂ አብረው መስራት አይችሉም"

እንደ ቋንቋ/ዘርና ሀይማኖት ወዘተ ልዩነታችን ሁሉ የአመለካከት ልዩነታችንም በጋራ ሀገራዊ ግንባታ ላይ ጥንካሬያችን ስለሆነ እጅግ አስፈላጊያችን ነው። … ይሁንና ኢትዮጵያውያን በትንሹም ይሁን በትልቁ በማንኛውም ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ ዘወትር በከፋ የአለመግባባት ልዩነት (ቅራኔ) ውስጥ ስለምንገባ፥ በህብረት (በአንድነት) ለመስራት ፈፅሞ አለመቻላችን … ከመጥፎ ባህርይነት ወደ መጥፎ ፖለቲካ ባህልነት እየተቀየረ መጥቶአል … የኢትዮጵያ ህዝብ ለሺ አመታት የዘለቁ ታላላቅ ቀደምት ሀይማኖቶች ተካታይ እንደመሆኑ መጠን … ከእኛ በላይ በጥሩ ስነ ምግባር የታነጸና ደግሞም ባለታሪክ ህዝብ በአለም ላይ የሚገኝ አይመስለንም … ነገርግን እኛ እንደምንለው ሳይሆን፤ ትላንትና ነጻነታቸውን ያገኙ ሀገሮች በአጭር ዘመን ውስጥ የማደጋቸውን ምስጢር የእኛን ያለማደግ ምክንያት፥ ያጋለጣል።

ነጻነታቸውን ካገኙ 50 (ሀምሳ) አመት የሞላቸው ሀገሮች ከሞላ ጎደል በስምምነት ሰርተው ለውጥ ሲያመጡ፥ … እኛ ሺ አመታት ቀደምት ብንሆንም ተስማምተን በጋራ ለመስራት ባለመቻላችን፥ … ዛሬ በአለም ላይ ከ 1 ሀገር በስተቀር የምንቀድመው የለም፡፡ … እርግጥ በጋራ ጠላት (የጦርነት ታሪኮች) ውጤታማነት በአለም የታወቅን ለመሆናችን ምንም ጥርጥር የለውም። … ነገር ግን ወደ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ስንመጣ የአለም መጨረሻ ነን ... ይህም “እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ" ፖሊሲያችን ውጤት ነው … በዋናነትም መሪዎቻችን ለእግዚአብሄርም ለህዝብም ባስቸገረ ማንነት፥ ያለ ህዝብ ፍላጎት ተጭነው በመግዛት፥ ሀገርን በፍትህ በመምራት ወደ ብልፅግና ለማምጣት አለመቻላቸው ... በስልጣን በመሻኮት እጅግ በከፋ የጥላቻና የቂም በቀል ኩሬ ውስጥ በመዘፈቅ … እርስበርስ በመጠፋፋት ፖሊሲያቸው፥ በጦርነት በመጠመድ አንደኛው በሌላኛው ላይ ስልጣኑን በሀይል ለመመስረት በሚያደርገው ትግል፥ ትውልዶች በጦርነት እሳት በከንቱ አለቁ፥ … የሀገሪትዋ ሀብትም ወደመ፥ … መልካም አስተዳድር በማጣት ምክንያት የመጡ 3 ቀውሶች በቀላል ምሳሌዎች: -

1- ኢኮኖሚ

ለሺ አመታት በ1 ማረሻ በበሬ እያረስን የሺ አመታት የጦርነት ታሪካችንን እንደ ሀገራዊ ልማት ለዘመናት ስንደልቅ … ነጻነታቸውን ካገኙ 50 (ሀምሳ) አመት ያልሞላቸው የአፍሪካ ሀገሮች ቢያንስ ከርሀብ ወጥተዋል። … እኛ ግን አሁንም ድረስ እንራባለን ... በFAO የ2013 መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ በየኣመቱ ባማካይ ከ16 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የምግብ እህል እርዳታ ጠባቂ ነው ... ከህዝባችን 93% የሚሆነው ለመኖር የሚያስፈልጉት ሶስት 3 መሰረታዊ ነገሮች፥ (በቂ ምግብ ልብስና መጠለያ-ቤት) ሳይሟላለት የሚኖር ነው። … በምግብ ራስን ያለመቻል ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የስልጣኔ መሰረት የሆነውን የቴክኖሎጂ ልማት ብንመለከት፥ በአፍሪካ ሀገሮችና በኢትዮጵያ መካከል ለምሳሌ … በኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት፥ … በኢንተርኔት አቅርቦት፥ በስልክ አቅርቦት … በመኖርያ ቤትና … በንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት … ከፍተኛ ልዩነት አለ።

2- ከፍተኛ ትምህርት

የኡጋንዳው ማካራሬ ዩኒቨርስቲ ከተመሰረተ 115 አመታት ያለፈው ሲሆን … የእኛው “አንጋፋ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግን ገና 65 አመት አካባቢ ነው። … በዚህ መሰረት ትላንትና ነፃነቷን ካገኘችው ኡጋንዳ ጋር ስንወዳደር … ለ50 አመታት (3 ትውልድ ያህል) ከከፍተኛ ት/ርት ወደሁዋላ እንድንቀር ተደርጓል … ከኡጋንዳ አንጻር እንኳን ስንወዳደር የመጀመሪያው ትውልድ ከ120 በፊት ኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ መግባት የነበረበት ሲሆን … “አንጋፋው” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በአሁኑ ሰአት 3ኛ ትውልድ ሳይሆን ቢያንስ 6ኛ ትውልድ በማስተማር ላይ መገኘት ነበረበት። … ከ120… 150… አመታት በፊት ኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ የገባ የመጀመሪያ ትውልድ ቢኖረን ኖሮ የተሻለ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ይኖረን ነበር፡፡

3- ፖለቲካ

የፖለቲካ ባህላችን የጦርነት ታሪክ ነው … በፖለቲካ ሹኩቻ አዲስ ገቢው መንግስት በአሮጌው መንግስት መቃብር ላይ የቀድሞውን እያፈረሰ የራሱን አዲስ አገዛዝ በሀይል የሚመሰርትበት ... ዘላቂ ሰላም ብልፅግናና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን በመከባበርና በማቻቻል ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ድርድር የማይደረግበት … ዛሬም በግሎባላይዜሽን ዘመን “…የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበጅ የአውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጅ…” የሚለውን ጥንት የተላለቅንበትን የመጠፋፋት ዘፈን የምናቀነቅን በመሆኑ የፖለቲካ ባህላችን በሽተኛ መሆኑን ያጋለጣል። … (ይህ ግን ህዝባችን በአለም የተደነቀበትን በአንድነት በሰላምና በፍቅር በሀይማኖት ተቻችሎ ተከባብሮ የሚኖርበትን ፅናት አይመለከትም)

ብሄራዊ መግባባት (National Consensus)

በአለም 'አንጋፋ የታሪክ ባለቤትነት' 'በሀይማኖት በስነ ምግባር በመልካም ሰብእና በመታነፅ' 'በሰው አክባሪነት' 'በእንግዳ ተቃባይነት' ወዘተ ቅፅሎች ሁሉ እንዳሉ ናቸው ብንል … ይህ ማንነት ግን ተግባባተን በጋራ ለመስራት አላስቻለንም። … ባህርያችን በስራችን መሆኑን አላስተዋልንም … የአለመተማመን ክስረት ውስጥ የገባ እንደ እኛ አይነት ህዝብ በአለም ላይ ያለ አይመስልም … የምንከተለው ሀይማኖትም ስለ ፍቅር ቢሰብክም፥ … ፍቅራችን ግን የግብዝነትና የለበጣ በመሆኑ፥ በፍቅር መሸናነፍ ቀርቶ ተራ ሰውኛ መግባባት ላይ እንኳን ለመድረስ አልቻልንም … የረዥም ዘመን ባለታሪክነትና ሀይማኖተኛነት በጋራ ጥቅማችን ላይ መስማማት የምንችልበትን አቅም ሊፈጥርልን አልቻለም … “ኢትዮጵያውያን አብረው መብላት እንጂ አብረው መስራት አይችሉም” የሚሉት ስድባዊ አባባል እርግጥም እውነትነት አለው፡፡

ብሄራዊ መግባባትን በተመለከተ ነግ በእኔ ነውና የኢህአዴግ መንግስት በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ሊባል የሚችል ያለጠላትነት በሰላም ለደርግ ባለስልጣናት ምህረትና ይቅርታ ማድረጉ በእጅጉ ያስመሰግነዋል፡፡ … ተጨማሪም ብሄራዊ መግባባት ለማድረግ 1ኛ/ከ40 አመታት ወዲህ የሞት የአካልና የንብረት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ካሳ መክፈልና ይቅርታ መጠየቅ ይገባል፡፡ … 2ኛ/ለፖለቲካ እስረኞች ምህረትና ይቅርታ ማድረግም ይገባል፡፡ … 3ኛ/ገዢውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች (በአይዲዮሎጂ ቢለያዩም፥ ተመሳሳይ የሀገር እድገት አላማ አላቸው) ብሄራዊ መግባባት ስለሌላቸው፥ ጦርነት ቀረሽ ፖለቲካዊ ጭቅጭቃቸው ፖለቲካዊና መረጋጋትና እድገት እንዳይኖር ያደርጋል ... ምሳሌ 1/ የባህር በር፥ … ጠ/ሚር መለስ "ወደብ ሸቀጥ ነው" በማለታቸው፥ ኢህአዴግ የባህር በር አጀንዳን የዘጋ ይመስላል፡፡ ... ተቃዋሚዎች ደግሞ “ሀገሪትዋ የባህር በር የማግኘት ህጋዊ፥ ታሪካዊ፥ ፖለቲካዊና አለም አቀፋዊ መብት አላት" ይላሉ ... ታዲያ ይሄን ተራራ የሚያህል የብሄራዊ ፖሊሲ ልዩነት ሳይፈታ (ብሄራዊ መግባባት ሳይኖር) ኢህአዴግ እራሱን ለማጥፋት ነው በምርጫ መሸነፍም ቢሆን የፖለቲካ ስልጣንን ለተቃዋሚ ፓርቲ የሚያስረክበው? … ምሳሌ 2/ የመሬት ፖሊሲ፥ … “መሬት የግል ይሁን የመንግስት?” የሚለው ብሄራዊ ጥያቄ በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በኢህአዴግ መካከል የሰማይና የምድር ያህል የሚራራቅ ፖሊሲ ልዩነት ሳይፈታ ነው (ብሄራዊ መግባባት ሳይኖር) ኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጣንን ለተቃዋሚ ፓርቲ የሚያስረክበው? ስለሆነም ብሄራዊ መግባባት የግድ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡

የኑሮ ልዩነት ችግርና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

ዛሬ ዛሬ አብረን ለመቁረስ እንኳን እንዳንችል የሰማይና የምድር ያህል ያራራቀን የገቢ ልዩነታችን ያስፈራናል … እንደቀድሞው ዘመን በጋራ የማንበላበት አንድ ምክንያት የሀብታችን ምንጩ ስለ"ማይታወቅ" ስለምናፍርበት ይሆን? … የደሀና የሀብታም የኑሮ ልዩነት እጅግ የመስፋት ችግር (Economic Inequality) በተመለከተ እጅግ በጣም ጥቂቶች (<0.0002%) ከአውሮፓ/ከአሜሪካ ስታንዳርድ (ደረጃ) በላይ ሲኖሩ … (93%) ህዝብ ደግሞ በእርዛት መኖር ሀገራዊ መሰረታዊ ችግራችን ነው። … በዚያች ደሀ ሀገር ውስጥ የገቢ ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል መራቅ ችግር … ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ችግር መኖር “… መንግስተ ሰማይም ሲኦልም እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው …” የሚሉን ደግሞ የውጭ ታዛቢዎች (ነጮች) ናቸው። … እንዲሁም የምግብ ዋስትና ችግር … የመልካም አስተዳደር ችግር (የፍትህ መዛባት ችግር) … የሙስና ችግር (ባቋራጭ ሀብታም የመሆን ችግር) … የስራ አጥነት ችግር … በመስፋፋቱ የተነሳ ህዝቡ ኑሮና ብልሀቱ እየተጣረሰበት በሰላም ሊኖር አይችልም። … የደሀና የሀብታም የኑሮ ልዩነት ችግር (Income gap) ለመፍታት ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል የግድ ስለሚያስፈልግ Tax & Economic Policy መሻሻል አለበት።

ድህነት አለመግባባትን ያባብሳል

አለመግባባታችንን ከሚያባብሱ ነገሮች ውስጥ ድህነት ዋነኛው ነው … ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ 100 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚኖራት ሲሆን … በአሁኑ ሰአት የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦትዋ ግን፤ ከ2ሺ ሜጋ ዋት የማይበልጥ በመሆኑ፤ … በዚህና በሌሎች የድህነት መስፈርቶችም ጭምር የድህነታችን ልክ ሲለካ … በአለም ላይ ከመጨረሻ 2ኛው እጅግ ደሃ ሀገር እንደሆንን በቅርቡ የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ በ2014/2015 ባደረገው ጥልቅና ሰፊ የጥናት መረጃ ጠቁሞኣል (Global Multidimensional Poverty Index (GMPI) www.ophi.org.uk) ። … ሀገሪቱ ግን የኤሌክትሪክ ሀይል ለአፍሪካና ለመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ኤክስፖርት በማድረግ በቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ የማግኘት አቅም አላት። … አባይ ቢገደብና 6ሺ ሜጋዋት በማመንጨት የኤሌክትሪክ ሀይሻሻ አቅማችንን ወደ 8ሺ ሜጋዋት ከፍ ቢል … 1ኛ/ የሀገር ውስጥ ሀይል ፍላጎትን በእጅጉ ይሻሻላል (ቢያንስ መብራት ተቋረጠብን ማለት ይቀራል) … 2ኛ/ የውጭ ኢንቨትመንት እንዲስፋፋ የኤልክትሪክ ሀይል አቅርቦት በእጅጉ ወሳኝ በመሆኑ … የውጭ ኢንቨስተር ከፖለቲካ መረጋጋት ቀጥሎ የሚጠይቀው … “ምን ያህል የኤሌክትሪክ ሀይል ኣቅርቦት አላችሁ?” መሆኑ … 3ኛ/ የኤሌክትሪክ ሀይል ወደ ውጭ ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማግኘት ሀገራዊ ግንባታና ተጨማሪ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ለማመንጨትም አባይ አስተዋፆው በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ነው።

ሌላው የድህነታችን ትልቁ መግለጫ የገቢ ንግድ (Import) እና የወጭ ንግዳችን (Export) ነው። … የኢትዮጵያ መንግስት የብሄራዊ ባንክ በ2012 /2013 ባወጣው የሀገሪቱ የገቢና የውጪ ንግድ ስታትስቲክስ መሰረት፤ የሀገራችን የገቢና የወጭ ንግድ ሬሽዮ (ንጽጽር) በአለም ላይ ካሉት የመጨረሻ ደካማ ሀገሮች ተርታ ነው። … ይኸውም ወደ ውጪ የምንልካቸው ምርቶች ከውጭ ከምናስገባቸው እቃዎች ጋር በዋጋ ሲነፃፀር Export ፡ Import ratio 1 እጅ ለ3 እጅ ነው … በአሀዝ ሲታይ በ2012/2013 ሀገሪቱ ወደ ውጭ የላከችው ምርቶች ዋጋ በድምሩ ወደ 3.5 (ሶስት ተኩል) ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ሲሆን፤ ከውጭ ያስመጣቻቸው እቃዎች ዋጋ ደግሞ በድምሩ ወደ 10 (አስር) ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል። … ስለሆነም በዚህ ስሌት መሰረት ከውጭ የምናስመጣቸውን እቃዎች ያለ ንግድ ጉድለት (Trade Deficit) ለማከናወን ወደ ውጭ የምንልካቸውን እቃዎች በመጠን በጥራትና በሽያጭ ዋጋ ከሶስት (3) እጥፍ በላይ ማደግ አለበት።

አባይ ለብሄራዊ መግባቢያነት

የአባይ ግድብ ግንባታን መቃወም ግን ምን የአይነት የፖለቲካ ስልት ነው? … እንዲያውም የአባይ ግድብ ግንባታ የከረረውን የጥላቻ ፖለቲካችንን ውጥረትን ያረግባል። … ስርነቀል የእድገት ለውጥ ለማምጣት የሀይል አቅርቦት በእጅጉ የሚያስፈልጋት ታላቅ ደግሞም ታናሽ ደሀ ደግሞም ሀብታም ሀገር ኢትዮጵያ በመንግስት ስታትስቲክስ መሰረት አሁን ባለችበት የ2ሺ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት፤ … እንኳን የውጭ ኢንቨስተሮችን ለልማት ለመጋበዝ ቀርቶ … የሀገር ውስጥ ፍጆታን ለሟሟላት ፈፅሞ አትችልም። … የአባይ ግድብ ግንባታ ለሀገሪትዋ ሁለገብ የልማት ስራዎች ዋና የሀይል ምንጭነት እጅግ መሰረታዊ ከመሆኑ በመለስ ለብሄራዊ ፖለቲካ መግባቢያነት ከሚረዱን ግብአቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን በቅንነት ያለመረዳት ችግር ያለ ይመስለኛል። … ምክንያቱም ይህንን የተረዳን ቢሆን ኖሮ ከቡድናዊ ፖለቲካዊ አመለካከታችን ውጭ መሆን ነበረብን። … ግድቡን ማንም ይገንባው ባለን አቅም መረባረብ እንጂ ገዢውን ፓርቲን ከመጥላት ችግር መያያዝ የለበትም። … ይልቁንም አባይ ቢገደብ ለብሄራዊ መግባቢያነት በር ይከፍታል ብሎ ማሰብ ይበጃል።

በማስተዋልና በጥበብ መመላለስ ማለት አባይን ተቃዋሚ-ፓርቲ ገደበው ገዢው-ፓርቲ ገደበው የተሰራውን ስራ መቀበል (acknowledge) ማድረግ ነው የሚገባው … በአባይ ግድብ ስራ መነሻነት በመከባበር ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ፖለቲካዊ ባህል ሊጀመር ይችላልና። … እውነትም አባይ ተገድቦ የኢትዮጵያ ህዝብም ተጠቅሞ፥ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ኢህአዴግም በፖለቲካዊ መቻቻል መልካም ግንኙነት ቢመሰርቱ  አባይ ለብሄራዊ መግባቢያነት ቢሆን ትልቅ ድል ታላቅ ገድልም ነው። … ስለሆነም አስተውለንና ተግባብተን በብሄራዊ ጉዳይ በጋራ ለመስራት ካልቻልን በስተቀር፥ አንድ የፖለቲካ ምሁር እንደጠቀሰው “If we are Political depressed, we will find it much harder to cope with political stalemates and our frustration lead us to wrong decision/action” በፖለቲካዊ ድንዛዜ ውስጥ ገብተናል፥ … ወይም ከጥንት የተጠናወተን የእርስበርስ ክፋት፥ ጥላቻና ቂም በቀል ዛሬም የግሎባላይዜሽን ዘመን ላይም አለቀቀንም? … ወይም ደግሞ ዘወትር “እኔ የምለው ብቻ ትክክል ነው” (My way is the Highway) የምንል ራስ ወዳድ ግትሮች ነን።

ምኑን አወቅን?

ጥላቻ በሰላም በጋራ ሊያኖር የማያስችል መርዝ … ቂም ወደ ተለመደው እርስ በርስ ጦርነት የሚወስደን አቋራጭ መንገድ … በቀል የህይወት መጋዝ መሆኑን በግሎባላይዜሽን ዘመን ካልተረዳን መቼ ነው የምንረዳው? … መልካም መንፈስና አእምሮ ያለው ሰው ምንጊዜም ገለልተኛነትን በማራመድ ሰውን ሁሉ እኩል የሚያይ ነው። … ከወገናዊነት ነፃ በመሆን ሚዛናዊ አስተሳሰብን የምናራምደው የጋራ ችግራችንን በጋራ በሰላም የምንፈታበት ሁሉም የሚያሸንፈበት (‘Win-Win Resolution') መንገድ ስለሆነ ብቻ ነው። … መቻቻልን ዛሬ ካልሰራን መቼ ነው የምንሰራው? የምንገኝበት ዘመንም ይህን ግድ እንደሚለን እንዴት አልተገነዘብንም? ... ይህንን ለማወቅም ሆነ መቻቻልን እውን ለማድረግ የአስተሳሰብ ልቀት የሚያስፈልግ ሲሆን … በአስተሳስብ ለመላቅ ደግሞ ‘MA’ ‘PhD’ ዲግሪ መጫን አያስፈልግም። … ጥላቻን ክፋትን ምቀኝነትን ስግብግብነትንና ምዝበራን ቂም-በቀልን ወዘተ በማስወገድ በምትካቸው ንፁህ አዕምሮና ንፁህ ልብን መፍጠር ብቻ ነው … በዚህም ከማይበጅ ጥላቻ አመለካከት ነፃ እንወጣለን።

ኦሮሚያንና ኦጋዴንን እንደ ኤርትራ ማስገንጠል ቀርቶ … ኤርትራም ኢትዮጵያም ኦሮሚያም ሱማሌም ጅቡቲም ሱዳንም ደቡብ ሱዳንም ኬንያም ኡጋንዳም የምስራቅ አፍሪካ ህዝብ ሁሉ… የጋራ ችግርን በጋራ ለመፍታት፤ … ከድርቅ (ርሀብ) ከጦርነት ነፃ ለማውጣት፤ ጠንካራ ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ ህብረት በመመስረት በሂደትም ፖለቲካዊ ቁርኝት በማምጣት በሰላም እና በብልጽግና የምንኖርበት ዘመንና ምድር መፍጠር ካላወቅን ምኑን አወቅን? … ዛሬም እንደትላንቱ ህዝቦችን በመከፋፍል የምናጋጭ ይህም ሁላችንንም ይዞ የሚጠፋ ስራ መሆኑንን ካላወቅን ምኑን አወቅን? ይህ የአእምሮ ጉድለት (Personality Disorder) መሆኑን ካላወቅን ምኑን አወቅን? … ዘላቂ ሰላም ለቀጠናው ማምጣትን ካላወቅን ምኑን አወቅን? ከአስተሳሰብ ድህነት ነፃ ካልወጣን ከኢኮኖሚም ሆነ ከፖለቲካ ድህነት ነፃ ልንወጣ እንደማንችል ካላወቅን ምኑን አወቅን? … በቋንቋና በባህላችን ራሳችንን በማስተዳደር፤ ለጋራ ጥቅምም አንድ በሚያደርጉን ጉዳዮች ላይ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ትብብር ማድረግ ካላወቅን ምኑን አወቅን? … ይህ ትውልድ ከመንግስቱ ሀይለማርያም፥ ከኢሳያስ አፈወርቂ ትውልዶች "ከራስ በላይ እግር" አስተሳሰብ ነፃ ካልወጣ ምኑን ነፃ ወጣ? … ከጥላቻና “እኔ የምለው ብቻ ትክክል ነው” አስተሳሰብ ነፃ መውጣት ዋና ነው።

በእውነት ገና ብዙ አልገባንም... የመንፈስና የአእምሮ ነጻነትን አልተቀዳጀንም፤ … የስሜታችን ባሪያዎች ስለሆን ሰዎችን ነፃ ልናወጣ ቀርቶ ራሳችንም ነፃ ሳንወጣ ዘመናችንን ጨርሰን ወደ መቃብር እንወርዳለን ... የመሬት ሆድ ውስጥ ገብተን ለዘላለም ፀጥ ከማለታችን በፊት ሰውን መውደድ ‘ሰላምና ፍቅር’ን መውደድ እንደሆነ በቅድሚያ እንወቅ። ... ፍቅርንና ሰላምን ካልሰበክን በስተቀር እንደለመድነው በማይጠቅም ደምሳሽ ጦርነት እርስበርስ መጠፋፋት ብቻ ነው ዛሬም ያለን አማራጭ። … የቱን እንምረጥ ሰላምን ፍቅርን ወይስ ጥላቻና ቂም-በቀል የሚወልደውን እርስበርስ መጠፋፋት? … ህዝቦችን አንዱን ብሄር ካንዱ፥ ኦሮሞን ከኣማራ፥ ትግሬንም አማራንም ከኤርትራ፥ ወዘተ እርስ በርስ ጠላት እንዲሆኑ ማድረግ ከንቱነት ነው። ... ከዚህ በኋላ "በጥባጭ እያለ ማን ንጹህ ውሃ ይጠጣል" እንደሚባለው አይነት ህይወት መኖር የለብንም። … ይህ ትውልድ በቅን አስተሳሰብ፥ በሰላም ወዳድነት፥ በጸዳ ኣእምሮ (Corruption free Mind) እንጂ በጉልበት (በጦርነት) የማያስብ መሆን ኣለበት።

ብናስተውል መልካም ይሆናል … ኣውቀንም ይሁን ሳናውቅ በሰራነው በደል ቀርቶ በተናገርንበት ነገር ሁሉ የምንጠየቅበት ዘመን ነው። … ሰው ከትግሬም፥ ከኤርትራም፥ ከአማራም፥ ከኦሮሞም ከየትም ይወለድ አመለካከት ባግባቡ በሰለጠነ መንገድ መተቸት አለበት። … "ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም ለመጪው ይታሰብበታል እንጂ” እንዲሉ መጭውን ዘመን እያሰብን እርስ በርስ መልካም እናድርግ። … ሁሉም ህዝቦች በሰላምና በብልጽግና ይኖሩ ዘንድ እንስራ … አንዱን አጥፍቶ ሌላውን ማልማት በግሎባላይዜሽን ዘመን አይቻልምና።

ገዢውና ተቀዋሚ ፓርቲዎች

1/ ተቃዋሚዎች ገዢውን ፓርቲ በዲሞክራሲ እጦት ምክንያት በመክሰስ አባይ እንዳይገደብ መከላከላችሁ የባህርይ ወይስ የፖለቲካ ችግር ነው? ... ከዲሞክራሲ እጦት ተቃዋሚዎች ነፃ ናችሁን? … ከፖለቲካ ስልጣን በፊት ዲሞክራሲን በመሀከላችሁ ለማስፈን ችላችሁዋልን? … ገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ስልጣን የሙጥኝ የሚልበት አንዱ ምክንያት፥ ስልጣን ቢለቅ የመኖር ዋስትና ከማጣት ቢሆንስ? … አሁን ባላችሁበት ደረጃ መስማማትና ዲሞክራሲን በመሀከላችሁ ማስፈንያ ልቻላችሁ፥ ስልጣን ብትይዙ እንዴት ነው ተስማምታችሁ ሀገር በሰላም ለመምራት የምትችሉት? … እንኳን በአሁኑ ሰአት በ1997 ታላቁ ምርጫ ተቃዋሚዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ለመረከብ “... የፖለቲካ ዝግጅት … ህብረት አንድነት የሌላችሁ ... መከናወን ያልቻላችሁ … ራስ-ወዳድ ግለኞች ግትሮች … በመሰነጣጠቅ የምትበታተኑ ‘አጥፍቶ ማሳያ’ መሆናችሁን አለምን የምታሽከረክረው ሁሉ በእጅዋ ሁሉ በደጅዋ አሜሪካ በአምባሳደርዋ Tibor Nagy በኩል የተናገረችው የሚከተለው ነው “… a serious opposition to exist, while the opposition will also have to be serious, instead of fractious, petty, selfish and generally irrelevant …” ተቃዋሚዎች በየጊዜው እንደ ጣቃ የምትሰነጣጠቁት የእከሌ ፓርቲ እንዲባል ነው እንዴ? … ተቃዋሚዎች ካለፉት መንግስታት አጥፍቶ መጥፋት ታሪክስ ተምራችሁዋልን? … ከስልጣን በላይ በመደራደር በመቻቻልና ተግባብቶም በመስራት ‘አጥፍቶ ማሳያ’ ከመሆን ስለምን ‘ሰርቶ ማሳያ’ አትሆኑም? … ምንም እንኩዋን ኢህአዴግ የያንዳንዱ ሰው ህይወት መሰረታዊ የኑሮ ደረጃ የለወጠ (Qualitative Life Change) ባያመጣም፥ … ለዘለቄታው ግን በያንዳንዱ ሰው ህይወት ላይ መሰረታዊ እድገት ለማምጣት የሚያስችል የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መንገዶች፥ ት/ቤቶች፥ ባቡር ሀዲድ፥ የከተማ ልማት፤ የአባይ ግድብ ግንባታ ወዘተ (Quantitative changes) መሰረት መጣሉን (Economic growth) … ይህም ብሄራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ ያስችላል ብላችሁ በማመን … ከጥላቻ ፖለቲካ ይልቅ ከነጥፋቱና ድካሙ ኢህአዴግን በይቅርታ በመቀበል በጋራ መስራት ካልቻላችሁ ሰላማዊ የፖለቲካ ስልጣን እንዴት ትረከባላችሁ? … ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን ተቀዋሚዎች እርስበርስ በመግባባት ዘላቂ አንድነት ፍጠሩ … ጠንካራና ትልቅ የፖለቲካ ፓርቲ ፍጠሩ።

2/ ገዢው ፓርቲ ሩብ ምእተ አመት ያህል በስልጣን ላይ ቆይቶ ሳለ ዛሬም “ዲሞክራሲ የሚገነባው በሂደት ነው” ሲል ይህ ስልጣን ላይ የመቆየት ፍላጎቱን እንጂ ለዲሞክራሲ ስረአት ግንባታ ቁርጠኛነቱን እንዴት ያሳል? … ኢህአዴግ “ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ያስፈልጋል” “የዲሞክራሲ ጥያቄ ከመብትም በላይ የህልውና ጥያቄ ነው” ብሎ ከመናገሩ አንጻር ‘ለመድብለ ፓርቲ ስረአት ግንባታ’ ቁርጠኛነት አሳይቶአልን? … ከተቃዋሚዊቾ ጋር ለመደራደር ኢህአዴግ የምሁራን እጥረት አለብኝ ብሎ ይሰጋ ይሆን እንዴ? … በ1997 የምርጫ ክርክርን እንዳየነው ከሆነ 'አብዮታዊ ዲሞክራሲ' የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ከጠ/ሚር መለስ በስተቀር የትኛውም የመንግስት ባለስልጣን የገባው አይመሰልም … በፖለቲካ ክርክሩ ወቅት የመንግስት ባለስልጣን ሲንተባተብ ነው የታየው። … ኢህአዴግ ያለበት ሁኔታ ተስማምቶኛል ብሎ ያምናል? የኑሮ ውድነትና የተተኪው ትውልድ ስራ የማጣት ችግር ብቻ የህዝብ ብሶትን በማባባስ በሂደት መሰረት ያናጋል ብሎ አይሰጋም? … በአባይ ግንባታ የህዝብን ልብ ከማግኘት የሀይል አድቫንቴጅ ፈጽሞ የሚልቅ ዘላቂ ውጤት ያለው ‘ብሄራዊ መግባባት’ በማድረግ የዲሞክራሲያ ግንባታ መስረት በመጣል በሙሉ ሀይል ሀገር መገንባት አይቻልም ብሎ ያምናል? … ብሄራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ ከማሳደድ ፖለቲካ Exclusive Policy/politic ይልቅ በፖለቲካዊ መደራደር ሁሉን በማሳተፍ Inclusive policy መስራት ካልቻለ ኢህአዴግ በዘላቂነት እንዴት ይኖራል?

ገዢው ፓርቲና ተቀዋሚ ፓርቲዎች … ከአባይ ግድብ ግንባታ በፊት “ዲሞክራሲ ይገንባ” … “ከዲሞክራሲ በፊት ታላቁን ጠላት ድህነትን አስቀድመን እንዋጋ” … “ዲሞክራሲ እህል ከጠገብን በሁዋላ” መባባላቸው … በቡድናዊ ፓርቲ አጀንዳ በመወጠር … በእርስበርስ ጥላቻ ክፉትና ቂም በቀል በመገፋት … አንዱ ላንዱ እንቅፋት ከመሆን ይልቅ በታላላቅ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ብሄራዊ መግባባት (National Consensus) በመፍጠር በጋራ በመስራት … ከፖለቲከኛነት ይበልጥ የህዝብ አጋርነታቸውን ማሳየት አለባቸው። … ጠ/ሚር ሀ/ማርያም “ለጋራ ሀገራችን በጋራ እንወያይ የሚል ጥሪ ማድረግ እፈልጋለሁ” ጥሪ ተቀዋሚ ፓርቲዎች መልስ መስጠት አለባችው። … ሀገሪትዋ ‘በEthnic based Federalism’ አደራጃጀትና ‘በCentral Government (non-federal-government) ሁለት ጫፎች የፖለቲካ አመለካከት ተወጥራለች። … የሚያዋጣው 'ብሄራዊ መግባባት' ነው። … ስለሆነም ህወሀት/ኢህአዴግ ልቡን አስፍቶ በመቻቻልና በመደራደር … የፖለቲካ ስልጣን በሀይል መያዝ ያበቃ ዘንድ የ'ብሄራዊ መግባባት' መድረክ በማዘጋጀት ጥሪ ማድረግ አለበት።

ግንዛቤ እጦትና ጭፍን ተቃውሞ

ያለን ግንዛቤ የተዛባ በመሆኑ እንቃረናለን … 1/አባይ አለም አቀፍ ወንዝ በመሆኑ ከተፋሰሱ ሀገራት በተጨማሪ በመካከለኛው ምስራቅ አረብ-እስራኤል ላይም ጂኦ-ፖለቲካዊ ተፅእኖ ያለው መሆኑን እየተረዳን በአለመረዳት እንቃረናለን … 2/አባይ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ኩራት የሚሆነው ስንጠቀምበት እንጂ አሊያ ኩራትነቱ ለግብጽ መሆኑን እየተረዳን በአለመረዳት እንቃረናለን … 3/አባይ አንድነታችንን የሚያስጠብቀው በጋራ ለጋራ ልማት ሲውል እንጂ በዘፈን አለመሆኑን ዛሬም ድረስ እየተረዳን በአለመረዳት እንቃረናለን … 4/በአለመግባባታችን ምክንያት ምናልባት አባይ ሊገነባ ባይችል ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ችግራችንን እየተባባሰ እንጂ እየተሻሻለ የሚመጣ አለመሆኑን በአለመረዳት እንቃረናለን … 5/ከሰሀራ በታች የአባይ ተፋሰስ ሀገራት በአለም ላይ እጅግ ድሀ ሲሆኑ … የአባይ ግድብ መሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በማምጣት የጋራ ልማትን የሚያፋጥን መሆኑን በአለመረዳት እንቃወማለን … 6/በአለም ላይ በፖለቲካ አለመረጋጋቱ የሚታወቀውን የአፍሪካ ቀንድ የአባይ ግድብ ዘላቂ ልማትና የንግድ ትስስር እንዲኖር በማድረግ የፖለቲካ መረጋጋት ሊያመጣ የሚችል መሆኑን በአለመረዳታችን እንቃወማለን።

EPRDF: too Big to Fail

አንዳንድ ሰዎች የሚያሳስባቸው ህወሀት/ኢህአዴግ እንዴት በሀይል ስልጣን ሊለቅ እንደሚችል ሲሆን፥ ኢህአዴግ በሀይል ስልጣን ቢለቅ ተያይዞ የሚመጣው ሀገራዊና አህጉራዊ (የአፍሪካ ቀንድ) ከፍተኛ ቀውስና መዘዞቹ ግን ይበልጥ ያሳስባል። … ይህም የተለመደው የኢትዮጵያ መንግስታት ስልጣን በሀይል የመገለባበጥ ባህል … አዲስ ገቢው መንግስት በአሮጌው መንግስት መቃብር ላይ የቀድሞውን እያፈረሰ የራሱን አገዛዝ በሀይል በሚመሰርትበት ወቅት… በህዝብ ላይ የሚደርሰው ጥፋት … አመፅ … ግድያ …ከስፍራ ከስራና ከንብረት መፈናቀል እጅግ የከፋ ነው፥ … ይበልጥ ደግሞ በዚህ ዘመን ኢህአዴግ በሀይል እንዲወድቅ ቢደረግ ከሀይለስላሴና ከደርግ መውደቅ የበለጠ ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውሶችን የሚያመጣ፥ … በቀላሉ ሊታረቁ በማይችሉ ብሄራዊና ፖለቲካዊ ቅራኔዎች የታጨቁበት፥ … ማህበረሰባዊ ጉዳቱም የትየለሌ ነው… እንደ ምሳሌ ህወሀትንና (TPLF) ኦነግን (OLF) የብሄር ፖለቲካ ድርጅቶች ብንውስድ፥ ለ 40 አመት (ሁለት ትውልዶች) ያደረጉት ብሄር-ተኮር ፖለቲካዊ ትግል፥ የመጀመሪያው ሊባል የሚችል ፌዴራላዊት ኢትዮጵያን ፈጥሮአል ብቻ ሳይሆን፥ … TPLF/EPRDF መንግስት ሆኖ ሀገር ሲመራ ሩብ ምእተ አመት (ከአንድ ትውልድ በላይ) ሞላው፥ … ከዚህ የተነሳ በመላው ኢትዮጵያ ለማለት ይቻላል የብሄር ነፃ አውጭ ድርጅት የሌለበት ወይም ቢያንስ የብሄር ፖለቲካ ፓርቲ የሌለበት አካባቢ የለም። … የብሄር ፖለቲካ አደረጃጀት የህወሀት እና የኦህዴድ ኢሊቶች ፍላጎት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን 1/ገዢው ፓርቲ የ‘ብሄር ፖለቲካ አደረጃጀት’ን የትግል ውጤት እንደሆነ ማመኑ … 2/የብሄር ፖለቲካ አደረጃጀት ከአዲስ አበባና ከአማራ ህዝብ በስተቀር የአብዛኛው ህዝብ ፍላጎትም እየሆነ መምጣት ናቸው።

“ኢትዮጵያዊነት ዘር ነውን?” … አክቲቪስት ታማኝ በየነ ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ በአድዋ ድል ክብረ በአል ላይ በአብዮት አደባባይ እንደረደርው "ዘሬ ኢትዮጵያዊ ነው" አይነት ግጥምና … ወይም ደግሞ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያምና … በቅርቡም ደግሞ ዶ/ር ያእቆብ ሀ/ማርያም እንደተናገሩት "ለኢትዮጵያዊነት ሲባል ዘራችንን እንካድ” አይነት አባባል፥ … ከቀድሞዎቹ አምባ-ገነን መንግስታት ‘አንድ ሀገር' … ‘አንድ ህዝብ’ … ‘አንድ ባህል’ … ‘አንድ ቋንቋ’ (Central Government) የፖለቲካ አመለካከት … ብረትን ከብረት ጋር በሙጫ ለማጣበቅ የመሞከር ያህል ጥረት ከመሆን የሚያልፍ አይመስልም። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ዜግነት እንጂ ዘር አይደለምና … ለመሆኑ ጥናት ቢደረግ ምን ያህል ፐርሰንቱ ዘሩን/ብሄሩን ወይስ ኢትዮጵያዊነትን ያስቀድማል? … ዘሬ ‘ኦሮሞ’ ‘ትግሬ’ ‘ሲዳማ’ ወዘተ ሳይሆን “ዘሬ ኢትዮጵያዊ ነው" የሚል ይመስላችሁዋል? … የእኔን ትንሽየ ዳሰሳ እንደመነሻ ላቅርብ … አሜሪካ ለሚኖሩ ለተለያዩ 9 የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አባላት ላቀረብኩላቸው “ዘር/ብሄር ወይስ ኢትዮጵያዊነት?” የቱ ይቀድማል? ጥያቄ … አዲስ አበባ ተወልዶ ካደገው ከአንድ ሰው… ከአማራ ክልል ከመጣ ሌላ አንድ ሰውና …እንዲሁም ጥያቄውን ካልመለሰው አንድ ሰው በስተቀር የተቀሩት 6ቱ ሰዎች ‘ኢትዮጵያዊነት’ን ከብሄር/ዘራቸውን በፊት ለማስቀድም እንደሚቸገሩ (እንደማይችሉ) አረጋግጠዋል። … በዚህች ቀላል ዳሰሳዊ ጠቋሚ ናሙና መሰረት 66% ያህሉ ‘ዘሩን የማያስቀድም ኢትዮጵያዊነትን’ እንደማይቀበል ገልጾኣል። ... ከዚህ በመነሳት በዘር ላይ የተመሰረተ አደረጃጀት የማይሰራው ‘በአዲስ አበባና በአማራ’ ክልል ብቻ ይመስላል … (የአማራ ክልል የብሄር አደረጃጀትን እንደማይቀበል እንደአለ ሆኖ … ኢህአዴግ ባደረገው ጥናት 97% የአዲስ አበባ ህዝብ በዘር/ብሄር ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀት እንደማይቀበል በቅርቡ ኢህአዴግን የከዳው ሚ/ር ደኤታ ነግሮናል) … የአማራና የአዲስ አበባ ህዝብ ደግሞ ከሀገሪትዋ ህዝብ 1/3ኛ ወይም ከ30% በላይ አይወክልም። … አክቲቪስት ጃዋር መሃመድ በቅርቡ በሚድያ ላይ “... Oromo First ..." ያለውንና … ከጥቂት አመታት በፊት ደግሞ አንድ የ‘ኦነግ’ ወይም የ‘ኦህዴድ’ ካድሬ መሆኑን በውል ያልለየሁት ሰው "…ኦሮሞነቴን የማታረጋግጥ ኢትዮጵያ ሺ ቦታ ትበጣጠስ…" በማለት በጋዜጣ ላይ ያስነበበውንም ያስታውሱአል። … ስለሆነም... 1ኛ/ የኢህአዴግ የዘር ፖለቲካዊ አደረጃጀት ስር የሰደደ ስለሆነ … 2ኛ/ ከኢትዮጵያ ህዝብ 2/3ኛው (66%) ህዝብ 'ዘሩን ያስቀደመ ኢትዮጵያዊነትን' የሚፈልግ ከሆነ … 3ኛ/ ኢኮኖሚውን ከ50% በላይና ወታደራዊውን ክንፍ የሚቆጣጠረው ኢህአዴግ ስለሆነ ’EPRDF is too big to Fail’ ለማለት ያስገድዳል። … ነገርግን “ኢህአዴግ too big too fail” ስለተባለም እንዳይታበይ ያስፈልጋል … ምክንያቱም መፅሀፍ ቅዱስ “ትእቢት ውድቀትን ትቀድማለች” ይላል።

## 3ኛው ኣስተሳሰብ (Third Alternatives)

በአባይ ግድብ ግንባታ ጉዳይ ላይ ዶ/ር መረራ ጉዲና “የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለውጭ ሃይል መጠቀሚያ ለመሆን ይዘጋጃሉ የሚል ግምት የለኝም” … “አባይን በሚመለከት ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ ያነሰ የአገር ስሜት አላቸው ብዬ አልገምትም” እንደአሉት ሁሉም አባይን በጋራ ለመገንባት መነሳት ይገባዋል። … አባይን ለብሄራዊ መግባባት መሰረት ነውና። … አባይ ለጋራ አላማ በህብረት መስራት እንጂ … “ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ የተሻለ ብሄራዊ ስሜት አላቸው” … “ኢህአዴግም ከተቃዋሚዎች የተሻለ የብሄረሰቦች መብት ያስከብራል” ወዘተ የመሳሰሉት ተራ መነቃቀፎች “እኛ የምንለው” “እነሱ የሚሉት” ከሚባለው በግሎባላይዜሽን ዘመን ከማይሰራና አንደኛው ሌላውን ከሚያገልል የቡድን ኣስተሳሰብ ነፃ ወጥተን “የጋራ ውሳኔያችን ትክክል ነው” በሚለው 3ኛው ኣስተሳሰብ (Third Alternatives) መተካት አለበት።

ዲሞክራሲ ወይስ ልማት የቱ ይቀድማል?

በቻይና አንድ አውራ ገዢ ፓርቲ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ በመግዛት ላለፉት አስርት አመታት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ ቢችልም … ‘ዲሞክራሲ ልማትን’ ‘ልማትም ዲሞክራሲ’ን ሳይቀድም እጅ ለእጅ ተያይዘው ሳይነጣጠሉ ሲጓዙ ውጤታማ ለመሆናቸው ማስረጃው በማንኛውም መስፈርት የቻይናንና-የአውሮፓን የሩሲያንና-የአሜሪካንን የእድገት ደረጃ በማወዳደር መልስ ማግኘት ይቻላል። … ኢህአዴግ በ‘አብዮታዊ ዲሞክራሲ’ አይዲዮሎጂ የቻይናን የሚመስል ‘ልማታዊ መንግስት’ ተከትሏል። … የMACRO ኢኮኖሚ ለውጥ (Economic growth or Quantitative changes) አምጥቶአል … ነገር ግን የህዝብ ኑሮ እድገት (Qualitative Life Change) ባለመምጣቱ መንግስት በጣም በመስጋት Economic Policy ለውጥ ሊያመጣ ይገባዋል። … በሌላ በኩል ፕሬዚዳንት ኦባማ በአፍሪካ የጋና ጉብኝታቸው ወቅት “… Africa doesn't need strong Man, but strong civic institutions…” አፍሪካ "ጠንካራ መሪ" (አንባገነን ላለማለት) ሳይሆን ጠንካራ የህዝብ ተቋማት ነው የሚያስፈልጋት" ቢሉም … ጠ/ሚር ሀይለማርያም ደሳለኝ በቅርቡ በአሜሪካ ሀገር በ CNBC ቴሌቪዠን ቻናል በሰጡት ኢንተርቪው ላይ “ኢትዮጵያ አሁንም ጠንካራ እጅ (መንግስት) ያስፈልጋታል” (“Ethiopia still needs strong hand”) ብለው መናገራቸው ኢህአዴግ ከፖለቲካውም ይሁን ከኢኮኖሚውም ውስጥ በቅርቡ እጅን የሚያወጣ ባይመስልም… ኢህአዴግ “የዲሞክራሲ ጥያቄ ከሙብትም በላይ የህልውና ጥያቄ ነው” በማለት መስጋቱ መልካም ሲሆን ተቀዋሚ ፓርቲዎችን በመደራደር በመቀበል መስራት ካልቻለ ግን ዋጋ የለውም።

ጥላቻ-አልባ ገለልተኛ ሚድያ

ብሄራዊ መግባባትን ለማምጣት እንደ EBC (Ethiopian Broadcasting Corporation) እና እንደ ESAT (Ethiopian Satellite TV) ያንድ ወገን ያልሆነ ነገርግን ገዢውን ፓርቲንም … ተቀዋሚ ፓርቲዎችንም … ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በመቀበል በነፃ ኣእምሮ የሚያስተናግድ ጥላቻ-አልባ ነፃ ሚድያ ገለልተኛ ኢትዮጵያውያን ማቋቋም አለባቸው።

ለአባይ ግድብ የፋይናንስ ምንጮች

ለአባይ ግድብ ግንባታ ብድርም ይሁን እርዳታ በርግጠኛነት የሚገኝ ለመሆኑ ከግብጽ ዲፕሊማሲያዊ ጥረትና ውጤት አንጻር የተዘጋ ፋይል ይመስላል። … ሁሉም አማራጭ ከጠፋ በራሳችን አቅም እንሰራዋለን በማለት መንግስት ይውተረተራል። … እስካሁን ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ያህል (የግድቡን ወጭ 10%) ለመሰብሰብ እንደተቻለ ይፋ ሆኖአል። … በርካታ ኢትዮጵያውያን በተለይ በውጭ ሀገራት የሚኖሩቱ፥ ... “ስልጣን ላይ ያለው መንግስት አሰብን ያለድርድር ስለሰጠ ... አባይን ለመገደብ ሀገራዊ ሞራል ብቃትና ኢኮኖሚያዊ አቅም የለውም” … “አሁን ባለው ሁኔታ (trend) ህዝቡ ገንዘብ ዋጣቱን ያለማቋረጥ ቢቀጥል እንኳን 5 ቢሊዮን ዶላር ለግድቡ ስራ ለማጠራቀም ከአስር(10) አመታት በላይ ስለሚፈጅ ኢህአዴግና አባይ 0 ለ 0 ናቸው” ይላሉ። … በእኔ እምነት ግን ተቃዋሚው ወገን የአባይን ጉዳይ ለፖለቲካዊ ፍጆታ ለማዋል መሞከሩ አለማስተዋል ብቻ ሳይሆን ዝቅጠት ውስጥ መግባት ይመስለኛል። … የፋይናንስ አቅምን በተመለከተ ግን የራስን ቅሪት ባግባቡ በመጠቀም መፍትሄ ሊያመጡ የሚችሉ አምስት 5 ዋና ዋና የፋይናንስ ምንጭ አካላት ሊኖሩን ይችላሉ ብዬ በማመን የሚከተሉትን እጠቁማለሁ:-

ምንጭ -1- የሀገር ቤት ህዝብ

የሀገር ቤት ህዝብ እስካሁን ድርስ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ለማዋጣት ችሏል፥ … ከዚህ በተጨማሪ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ለማዋጣት ይችላል ብለን ብንገምት፥ ... በድምሩ አንድ ቢሊዮን ዶላር በማዋጣት የግድቡን ወጭ 20% ድርሻ በመያዝ የአክሲዮን ባለቤት ይሆናል ... ምንም እንኳን ህዝቡ ገንዘብ ተርፎት ሳይሆን ከጉድለቱ ቢሰጥም፥ ለአባይ ታላቅ ሀገራዊ ልማት በህብረት መረባረቡ ሁለት ጎን ጥቅም አለው፥ ... አንደኛው አባይ መልሶ የሚከፍል መሆኑ ሲሆን፥ … ሁለተኛው ደግሞ አባይ ሀገራዊ አንድነትንም በእጅጉ ማጠናከሩ ነው፡፡ ... ስለዚህ የሀገር ቤቱ ህዝብ ቀበቶንም መቀነትም ጠበቅ ማድረግ ያስፈልገዋል።

ምንጭ -2- ዳያስፖራ

ኣንድ ሚሊዮን የሚጠጋው ዳያስፖራ ቢግባባ ባማካይ 5 ሺ ዶላር በማዋጣት በድምሩ በ5 ቢሊዮን ዶላር አባይን ብቻውን ለመገደብ ይችላል። … ነገርግን ዳያስፖራ በትንሹ ባማካይ 1 ሺ ዶላር በድምሩ 1 ቢሊዮን ዶላር (የግድቡን 20% ወጭ ) በማዋጣት በኢንቨስትመንት አጋርነቱ ባለአክሲዮን ከመሆን በላይ ለሰላማዊ የመቻቻል ፖለቲካ በር ተከፈተ ማለት ነው።

ምንጭ -3- ኢንዳውመንት ፈንድ (EFFORT)

የትግራይ ኢንዳውመንት ፈንድ ጠንካራ መሆኑን በሚሰራቸው ታላላቅ ልማቶች እያሳየ ነው። … ስለዚህም ኢፈርት ለአባይ ግድብ ግንባታ አንድ ቢሊዮን ዶላር (የግድቡን 20% ወጭ ) ቢያዋጣ ትልቁ ኢትዮጵያዊ የኢንዳውመንት ፈንድ ሆኖ ብሄራዊ ታሪክ ይመዘገብለታል።

ምንጭ -4- ሼክ መሀመድ ኣላሙዲ

አላሙዲ በአለም ቱጃሮች 75ኛ ተርታ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን … በዘመናቸው አንድ ትልቅ ልማታዊ ስራ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰርተው ለማየት የማይጓጓ ሰው የሌለ አይመስለኝም። … በርግጥ ታዋቂ ሰዎችንና ዘፋኞችን ስለሚያሳክሙና ስለሚረዱ ለዚያም ምስጋና አለን። … ሀገራዊ ልማታዊ ስራን በተመለከተ ግን አላሙዲ እንደ ኣንድ ተራ ኢንቨስተር በሻኪሶ ብቸኛ የወርቅ ማእድን ማውጣትና ኤክስፖርት በማድረግ … በሊሙ በቴፒና በበቃ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች ላይ የቡና ምርት መሰብሰብና ኤክስፖርት በማድረግ … በሸራተን የሆቴል ንግድ ከመስራት በስተቀር የህዝብን አንጀት የሚያርስ … እርሳቸውንም እጅ-ሰባራ የማያደርግ መሬት ጠብ የሚል ስራ እየሰሩ እንደሆነ መረጃ የለኝም … ቢኖር ኖሮ አይደበቅም ይታይ ነብር። … በመሆኑም በእኔ እምነት አላሙዲ የህዝብ ልብ ውስጥ የሚገቡበት ዋና ስራ የአባይ ግንባታ አንዱ በመሆኑ በግንባታ ወጭው በሚገባ መሳተፍ አለባቸው። … ስለዚህም ሼክ መሀመድ ሳይበዛ በትንሹ ኣንድ ቢሊዮን ዶላር (የግድቡን ወጭ 20%) በማዋጣት እጣ ቢገዙ ህዝቡ 'እውነትም እኝህ ሰው' የሚል ይመስለኛል። … ከዚህ በተጨማሪም በግብርናው ዘርፍም በምግብ ራስን በመቻል ፕሮግራም ቢሳተፉ አላሙዲ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ወዳጅ በመሆን ስማቸውን በመልካም ስራ ለዝንተ አለም ተጠራ ማለት ይሄኔ ነው። … (አላሙዲ "መፃፍ እንጂ ቁጥር አታውቅም ለካ!" እንዳይሉኝማ አቅም አስልቼ ነው የፃፍኩት)

ምንጭ -5- ፍላጎትና አቅም ያላቸው ኢትዮጵያውያን

ቀሪውን ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የግድቡን ወጭ ( 20% ያህል) ፍላጎትና አቅም ያላቸው የሀገር ቤትና ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን አክሲዮን ለመግዛት ቢችሉ በድምሩ 5 (አምስት) ቢሊዮን ዶላር ከነመጠባበቂያው ግድቡን ያስጨርሳል … ኢትዮጵያም የኤሌክትሪክ ሀይል አቅምዋን በአራት እጥፍ በማሳደግ የልማት መሰረትዋን ጣለች ለማለት ያስችላል።

(ማጠቃለያ) "ፍቅር የህግ ፍጻሜ ነው"

አገራችን ያለችበትን የፖለቲካ ትኩሳት በመረዳት … ካለፉት የጠላትነት ስሜት የጎደፈ ፖለቲካ ታሪካችን በመማር … የአለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ ግሎባላይዜሽንን በማገናዘብ፥ …በተለይም ልዩ መታወቂያችን የሆነውን 'እርስበርስ የመጠፋፋት ፖሊሲያችን'ን በማስወገድ ብሄራዊ መግባባት ላይ በመድረስ ሀገራዊ እድገትን ቢጋራ የሚያራምድ የጋራ ብሄራዊ አጀንዳ ለመቅረፅ እራሳችንን እንታደግ… "ይህ የሚቻል አይደለም" ለምትሉ፥ … 'በፍቅር ከሆነ ሁሉም ይቻላል' … "ሁሉም ነገር በፍቅር በጦርነትና ትክክል ነው" የተባለው እኮ፥ የሰው ልጅ የጠብመንጃ አፈሙዝ ከተደቀነበት፥ ወይም ደግሞ በተቃራኒው በፍቅር ከመጡበት ምንግዜም ቢሆን ተሸናፊ ስለሆነ ነው። … ፍቅሩ ቀርቶ ቢያንስ ጥላቻና ቂም በቀልን ወደኋላ ትተን … እርስ በራሳችን ምህረትንና ይቅርታን በማድረግ ዘላቂ የጋራ ሰላምና ልማት ለማምጣት አሁኑኑ እንነሳ … ፈቃጅም ወሳኝም እኛው ስለሆንን፤ ይህንን እውን ለማድረግ ከልብ እልኸኛነት በስተቀር የሚያቅተን የለም … መፅሀፍ ቅዱስ "እምነት፥ ተስፋ፥ ፍቅር ሶስቱ ጸንተው ይኖራሉ፥ ከሁሉም ፍቅር ይበልጣል" (1ኛ ቆሮንቶስ 13፤ 13) እንደሚል 'በከፋው ፖለቲካችን ላይ ቤንዚን ሳይሆን ፍቅርን በመጨመር፥ ከህገ-እግዚአብሄርም ከህገ-ተፈጥሮም ሳንወጣ፥ … እራሳችንን እንታደግ።

ፍቅር ዝም ብሎ ከሜዳ ኣይመጣም፤ ፍቅርን ማምጣት ከባድም ቀላልም ነው። … ፍቅር የሚከብደው እልኸኛነትና ትእቢት ሲሞላብን ነው … ፍቅር የሚቀለው ደግሞ ከምህረትና ከይቅርታ ሲጀመር ነው … 'እልኸኛነትንና ትእቢትን' ከመረጥን መዘዙ ከባድ ነው፥ … መጽሀፍ "ትእቢት ውድቀትን ትቀድማለች" እንደሚል ከትእቢታችን ቀጥሎ ያለጥርጥር ውድቀታችን ያውም በውርደት ይመጣል። … ነገርግን 'ይቅርታና ምህረትን' ከመረጥን እዳው ገብስ ነው። … የፖለቲካ ባላንጣን እንደ ጠላት ላለማየት ‘መመነን’ ወይም ‘መመንኮስ’ አያስፈልግም። … ሰዎችን ለመውደድ ቢያስቸግር ቢያንስ ባለመጥላት የራስንም የባላንጣንም ደስታና ሰላም በመጠበቅ ለመጓዝ ግን ይቻላል። … መጽሀፍ "እርስበርሱ የሚቃረን መንግስት (ሀገር) አይጸናም" እንደሚል፥ መቃረናችን ባግባቡ ያለጥላቻና ቂም በቀል፥ ያለ እርስበርስ መጠፋፋትም፥ በመቻቻልና በመደራደር ብቻ ይሆን ዘንድ ግድ ነው።

በአለም ላይ ለጠላቶቻቸው ምህረትና ይቅርታ በማድረግ ያለጠላትነት በሰላም በጋራ የመኖር ጥበብ ሞዴሎች ከሆኑት መሪዎች ውስጥ ኔልሰን ማንዴላና ማህተመ ጋንዲ ምንግዜም ተጠቃሽ ናቸው። … ማንዴላ "ጠላትህን ውደድ" "ወንድምህ ቢበድልህ ሰባት ግዜ ሰባ ይቅር በለው" በሚሉት የመጽሀፍ ቅዱሰ መመሪያዎች መሰረት … በቄስ ዴዝሞንድ ቱቱ ምክር በመታገዝ ለግፈኞቹ ህዳጣን ነጮች ገዢዎች ታላቅ ምህረትና ይቅርታ አድርገው ደቡብ አፍሪካን የሁሉም እኩል መኖሪያ (የኢኮኖሚ እኩልነትን ሳይጨምር) በማድረግ ዲሞክራሲና ሰላምን አስፍነዋል። … ኔልሰን ማንዴላና ማህተመ ጋንዲ በሀገራቸው አስተማማኝ ሰላምና እድገት ለማምጣት የመረጡት ይቅርታና ምህረት ያለበትን የፍቅር ጎዳና ሲሆን፤ እንዳዋጣቸው የምናውቀው ዘላቂ ሰላምና ዲሞክራሲ በማስፈን በብልጽግና ጎዳና ላይ መሆናቸው ነው።

አንድ የእንግሊዝ ቄስ በአንድ ወቅት ለማህተመ ጋንዲ መፅሀፍ ቅዱስ ሲሰጣቸው … ጋንዲ "እናንተን (እንግሊዞችን) አልወዳችሁም ኢየሱሳችሁን ግን እወደዋለሁ" በማለት የመለሱት መልስ አስገራሚ ነበር፥ … እንግሊዞች መፅሀፍ ቅዱስን መሸከም እንጂ የሰላም ትእዛዛቱን … የፍቅር መንገድን ሲዘነጉት፥ ጋንዲ ግን የፍቅርና የሰላም መንገድን አሸናፊነት ተረድናውት ነበር፥ … ማህተመ ጋንዲም ይሁኑ ኔልሰን ማንዴላ የበርካታ ብሄረሰቦችና ሀይማኖቶች ሀገሮቻቸውን ከጥላቻና ከቂም በቀል ፖለቲካ ያፀዱት በሁለት ነገሮች ብቻ ነው … 1/በይቅርታ (Forgiveness) … 2/ገደብ በሌለበት ፍቅር ናቸው፥ … እኛስ? 'አሸባሪ' … ’ዘረኛ’ … ’ጠባብ’ … ’ትምክህተኛ’ … ’ነፍጠኛ’ … ’ተለጣፊ’ … ’ባንዳ’ … ’ጎበና’ ወዘተ በመባባል … አንዳችን አንዳችንን ለማጥፋት ስለት ከመሳል … ጦር ከመስበቅ፥ … በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ጥላቻ-አልባ የፖለቲካ ህይወት ወሳኝ በመሆኑ … በምህረትና በይቅርታ ታድሰን፥ በመቻቻል ተደራድረን፥ ፍትህና ነጻነት፥ ዘላቂ ሰላምና ልማት ማምጣት ግድ አይለንም? … ዘላቂና እውነተኛ ሰላም፥ ልማት ነፃነትና እኩልነት የሚኖሩት ፍቅር ሁሉን ሲያሸንፍ ብቻ ነው … ምክንያቱም ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነውና (ሮሜ ምእ. 13-10) … ”ቤት በጥበብ ይሰራል፥ በማስተዋልም ይጸናል፥”

danruth20002gmail.com

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
January 11, 2015